April 4, 2017

ትናንትና በመጽሐፈ ገጽ መዝገቤ (በፌስ ቡክ አካውንቴ) ይህችን አረፍተነገር ጻፍኩ፦

“አየ እናንተ!!! የአህያ ቁራ በመከፈቱ ተደነቃቹህ? ወያኔ እኮ የሆነ ቦታ የሰው ሥጋ የሚበሉ ማኅበረሰቦች ቢኖሩ የሰው ቁራ ከፍቶ የሰው ሥጋ ለእነሱ እስከማቅረብ ድረስ የሚሔድ አረመኔና ኢሞራላዊ (ኢቅስማዊ) ፣

ኢግብረገባዊ፣ ኢሃይማኖታዊና ኢባሕላዊ የወንበዴ ቡድን እኮ ነው! እስከ አሁን አታውቁም እንዴ? ስትገርሙ! ለገበያ አልቀረበም እንጂ ወያኔ እኮ ስንትና ስንት የሰው ቁራዎች አሉት!!!” ብየ፡፡ ታዲያ አንዱ ከዚህ በታች ያለውን አስተያየት ጻፈ፡፡

“አምሳሉ የአህያ ቁራ መከፈቱ እንዴት እንዲህ እንዳማረራቹ አልገባኝም። እናንተ ብሉ ልተባላችሁ፤ እረዱ አልተባላችሁ፤ እዩም አልተባላችሁ.... ታድያ ምን ያገባችኋል? በሬና በግ ታነክታላችሁ፤ ሱማሌ ክልል ደሞ ግመል ይበላሉ፤ ኩባ፣ ቬትናምና ቻይና ደግሞ አህያ ይበላሉ። ምን ችግር አለው?

አህያ ሸኾናው ድፍን ስለሆነ አይበላም የሚል ከሙሴ ጋር የተቀበረ ምክንያት አትስጠኝ። በሬ ከበላህ አህያ በምንም ነውር አይሆንም። ሳይንሳዊ ምክንያት የላቹም። አገሪቱ ደግሞ በሃይማኖት ሕግ አትተደርም። ቆሻሻ የሚበላ ሕዝብ ይዘን አህ ለምን ይሸጣል ስትሉ አታፍሩም። እሱን በልተን ከረሃብ በወጣን በማን እድል። ወያኔ ትምክተኛ የሚላችሁ እናንተን መሆን አለበት። ወያኔን ብጠላም ለናንተ ግን መድሃኒት ነው።” ብሎ ጻፈ፡፡ እኔም የሚከተለውን መለስኩለት፦

“”’@.... እንዳልከው ነው! ለሞራል (ለቅስም) ያለህ ዋጋና ግምት ምንም ወይም ባዶ ከሆነ ከዚህ የተለየ ሊሰማህ የሚችል ነገር አለመኖሩ የሚጠበቅ ነው፡፡ ለሞራል (ለቅስም) ክብርና ዋጋ ላለው ለሚሰጥ ለአንድ ዜጋ ግን የሀገሩ ባሕል የሚጸየፈውና “ነውር!” የሚለው ነገር በገዛ ሀገሩ በይፋ ሲፈጸም ሲያይ በቀጥታ ከሥነ ልቡና እስከ የሕሊና ሰላምና ምቾት በማጣት በመታወክ፣ ምግብ በሆዱ ውስጥ እንዳይረጋጋ በማድረግ ወይም በማስታወክ በመሳሰሉት ችግሮች ይጠቃል፡፡ ለዚህም ነው የሀገሪቱ ሕግ “ሕዝቡ ተቀብሎት ከሚኖረው ባሕልና አስተሳሰብ ውጪ የሆነና

የሚቃረን ተግባርን መፈጸም ወንጀል ነው!” ሲል የሚደነግገው፡፡

ወገኔ ቆሻሻ ላይ የወደቀ ምግብን እየተመገበ ያለውና በረሀብ አለንጋ እየተገረፈ ያለው ሀገሩን በመነጠቁ፣ በገዛ ሀገሩ ሠርቶ የመብላት፣ መጠለያ የማግኘት መብቱን በመነጠቁ፣ በመገለሉና የበይ ተመልካች በመደረጉ እንጅ የሚበላ በመታጣቱ፣ ዝናብ በመጥፋቱ አይደለም፡፡ ሀገራችን ካላት የውኃ ሀብት የተነሣ “የአፍሪካ የውኃ ማማ!” መባሏን አታውቅም? ችግራችን አንተ ያልከው አለመሆኑንማ ምግብ ከቆሻሻ ጋር ከመደፋቱ እኮ ማረጋገጥ ትችላለህ፡፡

ካፌ ውስጥ ተቀምጠህ ወይም በአንድ ሌላ ሕዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ ላይ ባለህበት ሁለት ዋልጌዎች ተነሥተው በግልጽ ወሲብ ሲፈጽሙ ብታይ ለሞራል (ለቅስም) ዋጋ ለማትሰጠው ላንተ ምንም ላይመስልህ ይችላል፡፡ እንዲያውም ትዝናናበትም ይሆናል፡፡ ሞራል (ቅስም) ላላቸው ሰዎች ግን ይህ ተግባር ፈጽሞ ሊታገሱት የማይገባና የሚቀፍ፣ በመመልከታቸው ብቻ ለአካላዊና ሥነ ልቡናዊ ሕመም ሊዳረጉ የሚችሉበት አስቀያሚ፣ አስጸያፊ፣ ቀፋፊ ተግባር ነው፡፡

ባጭሩ ለሰው ልጅ (ልብ በል ለሰው ልጅ ነው ያልኩት ለአራዊት አይደለም ያልኩት) ትልቁ ብቱና ንብረቱ የሁለንተናዊ ጤናውና የደኅንነቱ ዋስትና በሞራል (በቅስም) ሕጎች የሚጠብቀው የሕሊና ወይም የውስጥ ሰላሙ ነው፡፡ ይሄ ከሌለህ ታብዳለህ! ጤነኛ ወይም የተረጋጋ ሥነልቡና ያለህ ልትሆን አትችልም! ከአካልህ ተቀርም ሰው የሚያሰኝ የሰው ልጅ መለያ ባሕርያት አይኖሩህም፡፡

የሙሴ ሕግ ከሙሴ ጋር አልተቀበረም! የሀገራችን ሕዝብ ባሕሉ አድርጎት እየኖረበት እየተዳደረበት የነበረና አሁንም ያለ መሆኑን የማታውቅ ከሆነ ፈጽሞ አታውቀንምና እኛን በተመለከተ ምንም ነገር አትናገር እሽ? ወገናችን እንኳንና እርም የሆኑ እንስሳትን ለምግብነት ሊጠቀም ቀርቶ እልቂት ባደረሰብን ረሀብ ውስጥ ሆኖ እንደቅጠል እየረገፈ ባለበት ሰዓት እንኳ ከብቶቹን ለመመገብ የሚቀፈው የማይጨክን ከፍተኛ የሞራል (የቅስም) እና የሰብአዊነት ደረጃ

ላይ ያለ ክቡር ሕዝብ ነው፡፡ “” በማለት፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገብረ ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com

# ለአህያማ አልጮህም…! | ከመምህር ዘመድኩን በቀለ



April 4, 2017

ኢትዮጵያ ” የአህያ አራጆች ” ሀገር.! አዲሱ የእኛ የኢትዮጵያውያን መጠሪያ ስም ። እድሜ ለኢህአዴግ በዓለም መድረክ ገና ተአምር በመስራት ያስደምመናል ።

በእናታችሁ ለስመሳይና ወገኞች.! የአዞ እንባም አፍሳሾች ፤ ላም ባልዋለበት ኩበት ለሚለቅሙ ወገኖቼ እንዲያነቡት ይህንን ጦማሬን

አመሰግናለሁ.! ገለቶማ.! ያቐንእለይ.!

ላለፉት 27 ዓመታት በዘር ፣ በሃይማኖት ፣ በጎጥና በመንደር ሲከፋፍሉት ዝም ያለ ህዝብ ፤ ሀገሩን ቆርጠው ወደብ አልባ ሲያደርጉት ፣ በመንደር ፣ በሰፈር እና በጎጥ ከፋፍለው አስር ትንንሽ ቦታ ሲሸነሽኑት እያየ ዝም ያለ ህዝብ ፣ እውን ዲሞክራሲ ያለ መስሎት ባዶ እጁን ለተቃውሞ በመውጣቱ እና ጥያቄ በመጠየቁ ብቻ ለምን ተቃወምከኝ ፤ ለምንስ ጥያቄ ጠየቅከኝ ብሎ በየአደባባይ ያውም በጠራራ ፀሐይ አናቱን በጥይት በርቅሶ ሲገድለው ዝም ጭጭ ያለ ህዝብ ፤ በነሐሴ ድቅድቅ ጨለማ ዶፍ ዝናብና በረዶ እየወረደበት የመኖሪያ ቤቱን በላዩ ሲያፈርስበትና የጎዳና ተዳዳሪ ሲያደርጉት ዝም ጭጭ ያለ ህዝብ.! ።

በዓለም ላይ የሚገኙ ግብረ ሰዶማውያን በሀገራችን መዲና በአዲስ አበባችን በጁፒተር ሆቴል ተሰባስበው “በሸነና” በሉ ብሎ መንግሥታችን ሲያዝናናቸው እና ሲጋብዛቸው እያየ ዝም ያለ ህዝብ ፤ ይህን ነውርና ርኩሰት ለመቃወም በሆቴሉ ዙሪያ የተሰበሰቡትን 200 የሚሆኑ የካዛንቺስ ሰፈር ወጣቶችን ፌደራል ፖሊስ አፈር ከድሜ ሲያስግጣቸው እያየ ምንም ሳይናገር ዝም ጭጭ ያለ ህዝብ ፣ ሙስሊሙን ከመስጊድ ክርስቲያኑን በቤተክርስቲያን ከቤተመቅደስ ከነጫማው ገብቶ በወታደር ቆመጥና ሰደፍ ሲቀጠቅጥ እያየ ዝም ጭጭ ያለ ህዝብ.! ዋልድባ ሲታረስ ፣ ቤተክርስቲያን ከነ ታቦቱ በግሬደር ሲፈርስ ፣ የሃገር ቅርስ ሲመዘበር ፣ ታሪክ ሲሻር ሲረዝ ፣ሲደለዝ ፣ እያየ ዝም ጭጭ ትንፍሽም ያላለ ህዝብ ።

በዐማራ ፣ በኦሮሚያ ፣ በሱማሌና በአፋር ፣ በደቡብና በጋምቤላ ህዝብ በገዢው ፓርቲ አማካኝነት በጅምላ ሲጨፈጨፍ እያየ ዝም ያለ ህዝብ ፣ በጋዜጣቸው ላይ መንግሥቱን የሚተች ጽሑፍ ስላስነበቡን ብቻ አሸባሪ ተብለው ከሚወዷቸው ቤተሰቦቻቸው ተለይተው እድሜ ልክም እስራት ተፈረዶባቸው ከወኅኒ ሲወረወሩ እያየ ምንም ሰብአዊነት ተሰምቶት ትንፍሽ ያላለ ህዝብ ድንገት ዛሬ ተነስቶ ለአህያ ጥብቅና በመቆም ያዙኝ ልቀቁኝ ይልልኛል.!

እኛ እኮ መቼም ሲፈጥረን ጀምሮ ወገኞች እኮ ነን ። ኮማንድ ፖስቱን ፈርቶ ፤ በፌስቡክ ላይ የጻፍኩትን ይቅርና ላይክ ያደረግኩትን እንኳ አይቶ ቂሊንጦ ቢያስገባኝስ እያለ እስከዛሬ ድረስ በፌስ ቡክ ገጹ ላይ ዳሌና ሽንጥ ካልሆነ በቀር ሀገሩን በሚመለከት ፖስት ሳያደርግ የከረመ ሁላ ዛሬ ደርሶ በድንገት አህያ ሊታረድ ነው ፣ ሥጋውም ሊሸጥ ነው ብሎ የአዞ እንባውን ሲያወርድ ይውልልኛል ።

ፕሮፌሰር አስራት በቁም ታርደው ሲገደሉ ፣ እነ አሰፋ ማሩ በአደባባይ ሲረሸኑ ፣ ኦሮሞ በመሆናቸው ብቻ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ከዩኒቨርስቲ ሲባረሩ ፣ ሲታሰሩ ፣ ሲገደሉ ፣ ዐማራ በመሆናቸው ብቻ ብዙዎች ከየክልሉ ሀብት ንብረታቸውን ተቀምተው ፣ ሰብአዊ ክብራቸውን ተገፍፈው ፣ እንደእባብ እና እንደ ጠላት አናት አናታቸውን ተቀጥቅጠው ሲገደሉ ፣ ሲባረሩና ሲሰደዱ ፤ በጋምቤላ መሬታቸውን በሥርዓቱ ሰዎች መነጠቃቸው ፣ ለአረቦችና ለህንዶችም መሸጡም ሳያንስ በየእለቱ ታላላቆችን የሚገድሉ ፣ ህጻናትን ለባርነት የሚያግዙ ፣ ሀብት ንብረት በማጥፋት በአካባቢው እልም ፍጥጥ ያለና በገሃድ የሚታይ የዘር ማጥፋት ወንጀል በጋምቤላ በሚገኙ ዜጎቻችን ላይ ሲፈፀም እያየ ዝም ፣ ጭጭ የሚለው ይሄ ገራሚ ህዝብ ዛሬ ደርሶ አህያ ሊታረድ ነው እያለ እሪሪሪሪ ቡራከረዩ ያዙኝ ልቀቁኝም ይላል.!።

በአዋሳ የሲዳማ ህዝብ ፣ በኮንሶ ፣ በመላዋ ኦሮምያ በሱማሌና በአፋር በዐማራ ተራ በተራ ህዝብ ሲጨፈጨፍ እያየ ዝም ጭጭ ያለ ህዝብ ፣ በወልቃይት ማንነቴን አትቀሙኝ ባለ እንደ ዋልያ ዘሩ እንዲመነምን እየተደረገ ያለ ህዝብ መኖሩን እያየ ዝም ያለ ፤ በሀገሪቱ ውስጥ የበይ ተመልካች ሆኖ በረሃብ ማለቁንና አይኑ እያየ በቁሙ መሞቱን ሸሽቶ በባህርና በየብስ ጭምር እግሬ አውጪኝ እያለ የሚሰደደውን ህዝብ ፣ በስደቱም ወቅት የአረብና የሌሎች አፍሪካውያን መጫወቻ እየሆነ ፣ በአይሲስ ቢላዋ ፣ በባህር ሰምጦ ፣ በበረሃ በውሃ ጥም ፣ በወባና በጊንጥ እየረገፈ በዓረብ “ማዳሞች” አሰቃቂ መከራና ግፍ ሲደርስበት እያየ ዝም ጭጭ ያለ ህዝብ ዛሬ ለአህያ ጥብቅና ቆሞ በየፌስቡኩ ያጓራልኛል ። አስመሳይ ሁላ ፣ ዛሬ ነው እንዴ ነውር በሀገሪቱ የተከሰተው? ዛሬ ነው እንዴ ርኩሰት በኢትዮጵያ ምድር የታየው.?? ምነው በእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ባህታዊው በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በመሰዊያው ስር በፓትሪያርክ አባ ጳውሎስ አንጋቾች በጥይት ተደብድቦ የእግዚአብሔር ሰው ሲገደል የት ነበርክ .? ምነው በማእከላዊ ማሰቃያ እስርቤት በሴቶች ብልት ብረት በማግባት ፣ በወንዶቹ ብልትም ላይ ሃይላንድ ሙሉ ውኃ በማንጠልጠል የዘር ፍሬ በማምከን ኢትዮጵያውያን ላይ ዘግናኝ ግፍ ሲፈጸም የት ነበርን.? ፣ የናትናኤልን ጥፍር በቁሙ ሲነቀል ፣ ሀብታሙ አያሌው ያ ሁሉ ስቃይና መከራ ሲደርስበት. ፣ ታምመው ለሚሰቃዩት ለእነ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ፣ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ እና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን እንደ ሰው ህክምና የማግኘት መብታቸውን ተነፍገው ሲያሰቃዩአቸው የት ነበርን.? ምነው ጎበዝ ለአህያዋ የጮህነውን ያህል ጩኸት አልጮህን?? ምነው ጥቂት እንኳ ሰብአዊነት ሳይሰማን ትንፍሽ ሳንልም ቀረን.???

አረ እንዲያው ለመሆኑ እኛስ ለገዢያችን ኢህአዴግ ከአህያዋ ተለይተን የምንታይ ሰዎች ነን ወይ.? እንደሰውስ ቆጥሮን ያውቃል ወይ.? ጠግርሮ የሚጭነን ፤ በፈለገበት ሰዓት በፈለገበት ቦታ እንደአህያ የሚረግጠንና የሚነርተን አይደለንም ወይ? ። ያለፍርድ የሚያስርህ ፣ የለህግ የሚገድልህ ክብርህን መሬት ላይ ረግጦ እንድትልሰው እያደረገህ እያየህ ስለየትኛው ክብር ነው የምታወራው ። ነውር ሀገሩን ሞልቶት እያየህ ስለየትኛው ነውር ነው የምታወራው ። የ 10 እና የ 11 ዓመት እመቦቀቅላ ሴት ህጻናት ልጆቻችን ለአስነዋሪ የዝሙት ሥራ ጀንበር ባዘቀዘቀች ቁጥር በጎዳና ላይ ፍስስ ብለው እያየህ ፣ ከእነሱም መርጠህ ከፈለካት ሚጢጢ ጋር ተጋድመህ እያደርግ የምን ነውር ነው የምታወራው???? አልገባኝም.? በእውነት አልገባኝም ።

አህያስ በይፋ ታርዳ ነው ዜና ተሠርቶላት ፣ ጋዜጣዊ መግለጫም ተሰጥቶላት በህጋዊ መንገድ እኮ ነው ኤክስፖርት ትዳረጋለች ተብሎ የተነገረን ። እኛ ክቡር የተባልነው የሰው ልጆች አለን አይደለ እንዴ እህቶቻችንን ለባርነት በየጊዜው በመንግስታችን አማካኝነት ድህነትን ለማሸነፍ በቁማችን ዐይናችን እያየ ለየዓረብ ሃገራቱ ኤክስፖርት የምንደረግ ። እንዲህ ሲሆን ማን ተቃወመ.? ማን አይሆንም አለ.? ማንስ ድምጹን አሰማ.? ማንም ። እንግዲያው ቅናት ይመስልብናል.? በአህያ የቀናን ይመስላል ። ሀሀሀሀሀ።

ቆይቶ ደግሞ ጠብቁ ብቻ እነዚህ ሰዎች እድሜ ካገኙ አህያ አርዶ ወደ ቻይና መላክ ሳይሆን እዚሁ ለእኛ የአህያ ሥጋ ያለበሉን እንደሆነ ምን አለ በሉኝ ። ቻይናዎቹ እንደው በቅርቡ የሰው ስጋ በሰርዲን መልክ ወደ አፍሪካ ይልካሉ ፣ የፕላስቲክ ሩዝ እያመረቱ ለአፍሪካ ያቀርባሉ ሲበል ሰምተን የለ ። አዎ ነገ የኛንም ሥጋ በልተው ላለመሸጣቸው ምንም ዋስትና የለንም።

ለነገሩ አሁንስ ቢሆን የአህያ ሥጋ ላለመብላታችን ምን ዋስትና አለን ።አዳሜ በኮተቤና በቡራዩ የታረዱና በየልኳንዳ ቤቱ ከተሰቀሉ የጅብ ሥጋ እያማረጥክ ስትበላ ከርመህ.! ከውሻ ስጋ የተዘጋጀና መረቅ የበዛበት ቅቅል በዚሁ በምትኖርበት ከተማህ ስትጠጣ ከርመህ ፣ ሰጋቱራና ጀሶ ቀላቅለው ያዘጋጁትን እንጀራ ጣመኝ ድገመኝ እያልክ ስትሰለቅጥ እና ሰትወጥቅ ከርመህ ፣ ሸክላና በርበሬ ፣ ሙዝና ቅቤ ፣ ማርና ስኳር ስትውጥ ከርመህ ደርሰህ ልክ እንደ ተአምራዊና አዲስ ነገር እነዚህ ሰዎች ብቻ የአህያ ሥጋ እንዳያበሉን ስትል እንዲያው ትንሽ እንኳን አለማፈርህ ።

የማኅበረሰቡ የሞራል እሴት እንዲጠፉ ከተደረገ እኮ ቆየ ። አራስ ልጇን በየጥሻው ለጅብና ለውሻ ቀለብ የምትሰጥ ጨካኝ እናት በተፈጠረችበት ሀገር ፣ የ 60 ዓመቱ አዛውንት የ 6 ዓመት ህጻን አስገድዶ በሚደፍርበት ሀገር ፣ ልጅ አባቱን እና እናቱን በዘነዘና ቀጥቅጦ በሚገድልበት ሀገር ። ደርሰን ለአህያ መታረድ ስናዝን ይገርመኛል ። ደግሞ የኃዘናችን አይነቱ ግራ የሚያጋባ እኮ ነው ። አርሴናል ስለተሸነፈ ራቱን የማይበላ ፣ ማንቸስተር ስለተሸነፈ ከሥራ ገበታው የሚቀር ፣ ሮናልዶ እግሩን ወለም ስላለው ሲያለቅስ የሚውል ፣ ለሩኒ ሚስት እርግዝና ሲጨነቅ የሚከርም ፣ ለቼልሲ ማሸነፍ በየቤተክርስቲያኑ እየዞረ ስለት የሚሳል ፣ በባርሴሎናና በርያል ማድሪድ ደጋፊነት ምክንያት በሚነሳ ብሽሽቅ ምክንያት ጎራ ለይቶ የገዛ ወገኑን በጩቤ ሰቅስቆ የሚገድል እብድ በሞላበት ሀገር ለራሱ ማዘኑን ትቶ ለአህያ ያዝንልኛል?!! ።

ሞራል እኮ ቀረ ፣ በግልጽ በፓርላማ መታወጅ ፣ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ መውጣት ብቻ እኮ ነው የቀረው ። እስቲ የቴሌቭዥን ድራማዎችን እንመልከት። ካለ ሌብነት ፣ ከለ ዝሙት ፣ ካለመግደል ፣ ካለመዝረፍ ፣ ከለማጭበርበር ምን ያስተምሩናል??? ። ምንም ። ምንም ።

ዛሬ ነው እንዴ ደርሰን ቻይናን ባህል ደፋሪ ያደረግናት.? በመካነሰላም ፣ በጉጉፍቱ ፣ በጎጃምና በትግራይ ለመንገድ ሥራ መጥተው አህያ እና ውሻ እየገጩ ፤ ወደ ካምፓቸው

ወስደው ቅርጥፍ አድርገው ሲበሉ የት ነበርን ። በየመንደሩ እንደ እንደ ዶሮ እንቁላል በተለይ ከአማራ ሴት እንዲወልዱና ዘር እንዲቀይጡ ሲደረግ የት ነበርክ ። ምነው ያኔ ድምጽህ ተዘጋ.? ጠብቁ ደግሞ ምን አለ በሉኝ ቻይና ገና ጉድ ታፈላብናለች ። የአህያ

ታርዶ መሸጥ ሲገርማችሁ ገንዘብ ካየ መሸጥ ብቻ የሚታየው መንግሥታችን እኛኑ በቁማችን በመሸጥ ለእርድ ሳያቀርበን የቀረ እንደሁ ቱ ምንአለ በሉኝ ።

ከሁሉ ከሁሉ ደግሞ የሚያስቀኝ እና የሚገርመኝ ነገር ቢኖር ይህ የእርኩሰትና የሞራል ውድቀት የሚያመጡ ትውልድ ገዳይ የሆኑ ፋብሪካዎች ሁል ጊዜ የሚቋቋሙት ወይ በኦሮምያ ወይ በዐማራ ክልል ብቻ መሆኑ ነው ። ለዐማራ እንኳን እግዚአብሔር ይመስገን ሰካራም እንዲሆን ቢራ ፋብሪካ ብቻ ነው የሚከፈትለት ። አለ እንጂ ለኦሮሞ ህዝብ የተቆረጠ ጡት በሞሶቦ ሲሚንቶ ተገድግዶ የሚሠራለት ። ይሄ ሳያንስ የአህያ አንገት የሚቆርጥ ፋብሪካ ይኸው እዚያው በኦሮሞ መሬት ላይ ተከፍቶ አረፈለት ። በእሬቻ በአል ላይ በጅምላ ዜጎችን ማረድ ያልፈራ መንግሥት አህያና ውሻ አረደ ብሎ ጉድ ጉድ እያሉ ማላዘን ነውርም ፣ ኃጢአትም ነው ።

ከእንግዲህ ወዲያ በኢትዮጵያ የአህያ ሌባውም ይበዛል ፣ የትራንስፖርት እጥረትም ይከሰታል ። ከቄራ ታርዶ የሚመጣና በየልኳንዳው የሚሸጥ ሥጋስ ማን አምኖ ይበላል? ይሄ የእኔ ጥያቄ ነው ።

የሃይማኖት አባቶች ያስቆሙታል ብለህ እንዳትጠብቅ ። እነሱ እንዲህች አይነት ነገር ለመቃወም ቢሞክሩ አንበርክኮ ነው የሚገርፋቸው ። ጆሮ ያዙ ወላጅ አምጡም ብሎ ነው የሚያሰቃያቸው ። እንዲያውም የልማቱ አካል መሆናቸውን ለማሳየት ፋብሪካውን ሄደው እንዲባርኩስ ሳይደረጉ ፣ ሳይገደዱስ ይቀራሉ ብላችሁ ነው??

ባለፈው ጊዜ ግብረሰዶማውያን በአዲስ አበባ በተሰበሰቡ ጊዜ ነፍሳቸውን ይማርና በአባ ጳውሎስ የሚመሩ አራቱ የሃይማኖት ካድሬ አባት ተብዬዎች ወጉ አይቀርምና ጋዜጠኞች ጠርተው ፣ የአቋም መግለጫም በትነው ፣ መግለጫውን ሊሰጡ ሲል በዚያን ጊዜ በወቅቱ አቶ ቴዎድሮስ አድሃኖም ጋዜጣዊ መግለጫ መስጫው አዳራሹን በርግደው በመግባት እነ አባ ጳውሎስን በዚያ ሁሉ ጋዜጠኞች ፊት ፑሽ አፕ ፣ ቁጭ ብድግ የማሠራት ያህል አሸቀጥቁጠው የተበተነውንም ግብረ ሰዶማዊነትን የሚቃወመውን የአቋም መግለጫ ከየጋዜጠኞቹ እጅ ሰብስበው በመውሰድ ድምጽ ሳታሰሙ ሹልክ ብላችሁ ውጡ በማለት ጠፍጥፈው እንደስቆሙዋቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው ።

እንዲያውም ለዚያ ውለታ ይመስለኛል ዛሬ አቶ ቴዎድሮስ አድሃኖም በተቅማጥና በትውከት በኮሌራና በወባ እንዲሁም በኤች አይቪ ኤድስ ለሚረግፈው ህዝባቸው ምንም ያልፈየዱትን ሰው ለዓለም ጤና ጥበቃ ዳይሬክተርነት እንዲወዳደሩ እያደረጉዋቸው ያሉት ። እንደ አያያዛቸው ከሆነ አውቀው የሚሸነፉላቸው እየበዙ ነውና ለውለታቸው ሲባል ሳይመረጡ የሚቀሩም አይመስለኝ ። ውለታ እንዴት ይረሳል ።

እናም ጎበዝ መጀመሪያ እንደ አህያ የተቆጠርን እኛ ለራሳችን እንዘን ፣ ራሳችንንም በቅድሚያ ነፃ እናውጣና ኋላ ላይ ከዚያ በኋላ ለአህያዋ መብት በመጮህ አህያን ነፃ እናወጣታለን ። አይመስላችሁም ጎበዝ ። አራት ነጥብ ።

ይህንንም ራሴው በእጄ ጻፍኩት ። +4915217428134 ደግሞ የቫይበር ፣ የኢሞና የኋትስአፕ መልእክቶችን የምቀበልበት የእጅ ስልኬ ነው ።

ሻሎም.! ሰላም.!

ዘመድኩን በቀለ ነኝ።

መጋቢት /25/2009 ዓም

ከራየን ወንዝ ማዶ።

# መጀመሪያ ባለስልጣኖቹ የአህያ ስጋ መብላትን በደንብ እንደተለማመዱ ግንዛቤ ይያዝበት | ሸንቁጥ አየለ

April 3, 2017

ወያኔ የአህያ ስጋ በቻይና ነጋዴዎች በኩል ኤክስፖርት እንዲደረግ ሲፈቅድ የኢትዮጵያ ህዝብ መንፈሱ እንደ ሚበሳጭ : ልቡ እንደሚያዝን: የመዋረድ ስሜት እንደሚሰማዉና ተስፋ መቁረጥ እንደሚንጸባረቅ በደንብ ያዉቃል::የኢትዮጵያ ህዝብ እስላሙም ሆነ ክርስቲያኑ ወይም ሌላ እምነት ያለዉ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የባህል እና የመንፈሳዊ መሰረቱ ይሄን ነገር አጥብቆ የሚጸዩፈ እንደሆነ

ያዉቃል::ሆኖም ወያኔ ሆን ብሎ የኢትዮጵያ ህዝብን መንፈሳዊ መሰረተ ለማዋረድ ብሎም የባህል እሴቱን ወደ አልቦ ለመክተት ማንኛዉንም የጸረ ኢትዮጵያዊነት ስነልቦና የዉጭ ባህል እያመጣ ኢትዮጵያ ህዝብ መሃል ይደፋል:: በዚህም ህዝቡን ተስፋ እንዲቆርጥ: ከመንፈሳዊነት እንዲላቀቅ: ባህል የሌላዉ ህዝብ እንዲሆን : ስነልቦናዉ የተሳከረ እና ግራ የተጋባ እንዲሆን የመደላድል አዉድማዉን ይጥላል::



ኢትዮጵያዊነት የጋራ መገለጫ እሴቶች እና የጋራ ዉህድ መንፈሳዊ መሰረቶች እንዳሉት ብሎም እነዚህ ህዝባዊ መሰረቶች ህዝቡን እንዳስተሳሰሩት የሚያዉቀዉ ወያኔ ይሄን መሰረት መናድ እንዳለበት የወሰነዉ ጫካ ሆኖ ነዉ:: የዘራዉ የጎሳ ልዩነት: የሀይማኖት የእርስ በርስ መቃቃር: የታሪክ መቆሳሰል እና አለመተማመን ጭብጥ ብሎም የኢትዮጵያዊነት ህላዌን የመካድ ጥልቅ እርሾ የመጨረሻዉን ፍሬ የሚያፈራለት በኢንቨስትመንት እና በኢኮኖሚ ልማት ስም ኢትዮጵያዉያን ያላቸዉ መሰረታዊ የመንፈሳዊ: የባህል እና የስነልቦና እሴት ሁሉ ለመጨረሻ ጊዜ ተዋርዶ ሲበጣጠስ እንደሆነ አስልቶ የተነሳዉ ወያኔ ምናልባትም ወደፊት የሰዉ ልጅ ኩላሊት መገበያያ ማዕከል በገሃድ በሀገሪቱ እንዲኖር ሊፈቅድና ኢትዮጵያዊነት የመጨረሻዉ የባዶነት ስሜት ዉስጥ ጠልቆ እንዲገባ ሊያደርግ እንደሚችል ይታወቃል:: ለነገሩ ምን የቀረ ነገር አለ? ግን ብዙ የቀረ የኢትዮጵያዊነት እርሾ አለ::ወያኔ የማያዬዉ ::እኛ ኢትዮጵያዊያኖቹ ግን የምናዬዉ !

በነገራችን ላይ ከጥቂት አመታት በፊት ከተወሰኑ የወያኔ ባለስልጣኖች አንደበት በገሃድ የሚሰማ ንግግር ነበር::ይሄዉም ቻይና በሚሄዱበት ጊዜ አብዛኞች የአህያ ስጋ እየበሉ እንደመጡ በኩራት ይናገሩ ነበር::የፈረስ ስጋም በላን ሲሉ የተደመጡ ነበሩ:: ይሄን እኔ እራሴ በጆሮዬ ሁሉ ሰምቼ ዘግንኖኛል:: እንዴዉም በአንድ የግል ጋዜጣ ላይ "ባህል እና የአመራር ስልት" የሚል አንድ ጽሁፍ አቅርቤ ነበር::እናም መጀመሪያ ባለስልጣኖቹ የአህያ እና የፈረስ ስጋ መብላትን በደንብ እንደተለማመዱ ግንዛቤ ይያዝበት::

የብልጽግና ጽንሰ ሀሳብ ሊቃዉንቱ በስፋት አብራርተዉ እንደ ገለጹት ሁል አቀፍ ብልጽግና (holistic development) በአንዲት ሀገር ዉስጥ ሊኖር የሚችለዉ ባህልን: መንፈሳዊነትን: ማህበራዊ መሰረትን: ህግን እና ፍትህን: ተቋማትን: ታሪክን: ስነልቦናን: ኢኮኖሚን: ፖለቲካን: አካባቢን : የሰዉ ሀብት ብልጽግናን እንዲሁም ሌሎችንም ተያያዥ ጉዳዮችን ሁሉ ያካተተ እና ግንዛቤ ዉስጥ ያስገባ የተሳለጠ የብልጽግና ፖሊሲ እና እስትራቴጅ ሲኖር ብቻ ነዉ ::ወያኔ ይሄን በደንብ ያዉቃል::ግን እርሱ ግቡ ኢትዮጵያን ማብልጽግ ሳይሆን ራዕይዉ ኢትዮጵያን ወደ አልቦነት ደረጃ በማዉረድ የዘቀጠ ማህበረሰብ የሚኖርባት ለአገዛዝ የምትመች የጎሳ ስብስብ የሆነች ስመ ሀገር ማድረግ ነዉ::እሱ ያለ ተቀናቃኝ እየጨፈረ እንዲኖር መሆኑ ነዉ::

የዝንጀሮን ቅኔ እዚህ ማጣቀሱ ግን መልካም ነዉ:-

የእግዜርን ነገር ምኑን አዉቀሽዉ :

ወይ እኔ እበላዉ አንቺ አርመሽዉ !

እናዳለች ዝንጀሮ ይሄ ሁሉ ደባዉ እራሱን የሚያጠፋ ብሎም ምናልባትም ደግሞ ኢትዮጵያዉያንን ባልታሰበ ሚስጥራዊ ኩነት የሚያስተሳስር እልህን የሚያጭር እርሾ ሆኖ ሊወጣ ይችል ይሆናል::

# የበሬ ስጋ እየበላህ የአህያን ስጋ መከልከል አትችልም!

April 3, 2017

ከስዩም ተሾመ

“አህያ!” – “ደደብ፥ ደነዝ፥ የማይገባው” ለማለት፣ “በቅሎ አባትሽ ማን ነው ቢሏት አጎቴ ፈረስ ነው አለች” – ለአህያ ያለንን ዝግተኛ ግምት ያሳያል፣ “አህያ ሰባ ምን ሊረባ” – የአህያ ሥጋ እንደማይበላ ይጠቁማል፣ …ወዘተ። እድሜ ለአለም አቀፉ የገበያ ትስስር (Globalization)፣ በሀገራችን ክብር የተነፈጋት እና ዝቅተኛ ግምት የመሚሰጣትን አህያ የሚፈልግ እንግዳ ከሩቅ ምስራቅ ድረስ መጥቷል። የአህያን ሥጋ ቬትናሞች ለምግብ፣ ቻይናዎች ደግሞ ቆዳዋን ለመድሃኒት በጥብቅ እየፈለጉት እንደሆነ ሰሞኑን [ተሰምቷል](link)። ስለዚህ፣ እኛ የማንፈልገውን ፈልጎ ደጃፋችን ድረስ የመጣን እንግዳ በአግባቡ ማስተናገድ እንጂ ሌላ ሁኻታ መፍጠር ተገቢ አይመስለኝም።

በመጀመሪያ ደረጃ ነገሩ ሀገራዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም-አቀፋዊና አህጉራዊ ጭምር እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። በእርግጥ የአህያ ሥጋ ከቬትናም በተጨማሪ በቻይና እና አንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት ጭምር ለምግብነት እንደሚውል ይታወቃል። ነገር ግን፣ አህያን በጣም [ተፈላጊ ያደረጋት](link) ከሥጋዋ ይልቅ ቆዳዋ ነው። በቻይና የአህያ ቆዳ በጣም ተፈላጊ ነው። ምክንያቱም፣ ቻይናዊያን የአህያን ቆዳ በመቀቀል ከውስጡ ¨gelatine” የተባለ ንጥረ ነገር የሚያመርቱ ሲሆን ይህ ደግሞ ”Ejiao” ለተባለው የቻይና ባህላዊ መድሃኒት ዋና ግብዓት ሆኖ ያገለግላል።

Hundreds of donkey skins drying in the sun as part of the production process of ejiao. Global demand is estimated between 4 to 10m skins per year.

በቻይና የአህያ ቆዳ ተፈላጊነት እንዲጨምር ያደረገው መካከለኛ ገቢ ያላቸው የሀገሪቱ ዜጎች ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት መጨመሩና ስለ ”Ejiao” ፍቱን መድሃኒትነት በሚቀርቡ የማስታወቂያ ሥራዎች እንደሆኑ ዘገባዎች ያስረዳሉ። ዛሬ በቻይና አንድ ኪሎ ግራም “Ejiao” እስከ £300 ፓውንድ በሚደርስ ዋጋ ይሸጣል። በዚህ ምክንያት በቻይና የአህያ ቁጥር እ.አ.አ. በ 1991 ከነበረበት በእጥፍ መቀነሱን [ዘገባዎች](link) ያስረዳሉ። በዚህ ምክንያት በዓለም አቀፉ ገበያ ውስጥም ከፍተኛ የሆነ የፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠን ተፈጥሯል። ለዓለም ገበያ በአንድ አመት ውስጥ 1.8 ሚሊዮን የአህያ ቆዳ ለሽያጭ የሚቀርብ ሲሆን ዓመታዊ የገበያ ፍላጎቱ ግን 4 እስከ 10 ሚሊዮን ሊደርስ እንደሚችል ይገመታል።

የአህያ ቆዳ ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ ምክንያት፣ ለምሳሌ በቡርኪና ፋሶ የአንድ አህያ የመሸጫ ዋጋ እ.አ.አ. 2014 ከነበረበት 60 ዶላር ወደ 108 ዶላር ጨምሯል። እንደ ግብፅ፣ ደቡብ አፍሪካና ታንዛኒያ ባሉ ሀገራት ደግሞ አህዮችን ለቆዳቸው ሲባል በሕገወጥ መንገድ መስረቅና በየስርቻው ማረድ እንደተጀመረ አንዳንድ [ሪፖርቶች](link) ይጠቁማሉ። በአህያ ብዛት በአፍሪካ ቀዳሚ በሆኑት ኬኒያና ኢትዮጲያ ደግሞ በመንግስት እውቅና የተሰጠው የአህያ ማረጃ “ቄራ” ተከፍቷል።

ሰሞኑን ከወደ ቢሾፍቱ (ደብረዘይት)የተሰማው ዜና ከላይ የተጠቀሰው አለም አቀፋዊና አህጉራዊ እውነታ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። በዘገባው መሰረት፣ በቢሾፍቱ ከተማ በ 80 ሚሊዮን ብር ወጪ “የአህያ ቀራ” መገንባቱ እና የአህያ ስጋና ቆዳን ወደ ዉጪ መላክ ሊጀመር እንደሆነ ተገልጿል። ከዚህ በተጨማሪ፣ [ሌላ የአህያ ቄራ](link) በኦሮሚያ ክልል፥ አርሲ ዞን፥ አሰላ አከባቢ በቻይናዊያን ባለሃብቶች እየተገነባ እንደሆነ ተጠቅሷል።

ከላይ የተጠቀሰው ዜና ሰሞኑን በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ መነጋገሪያ ርዕስ ሆኖ ሰንብቷል። “የአህያ ስጋና ቆዳ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በሀገራችን ሊከፈት አይገባም”፣ “ፋብሪካው እንዲከፈት በመፍቀድ መንግስት የሀገሪቱን ሞራላዊ እሴት ጥሷል” እና የመሳሰሉት ዓይነት አስተያየቶች በስፋት እየተደመጡ ይገኛል። ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ ከጥቂት ወራት በፊት በቢሾፍቱ የተገነባው ፋብሪካ የዚህ ዓይነት አመለካከት ባላቸው ሰዎች በእሳት ተለኩሶ እንደነበር [ዘገባዎች](link) ያስረዳሉ።

በእርግጥ የአህያ ስጋን አለመብላት መብት ነው። ሌሎች ሰዎች እንዳይበሉ መከልከል ግን ወንጀል ነው። በዚህ መሰረት፣ ከላይ የተጠቀሰው ድርጅት የተቋቋመበትን ዓላማና ተግባር እንዳያከናውን እንቅፋት መሆን ከሞራልና ኢኮኖሚያዊ መርህ አንፃር ተቀባይነት የለውም። ለዚህ ደግሞ ሦስት መሰረታዊ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል።

**1 ኛ)** የጅብ ቆዳን እየገዛን የአህያ ቆዳ እንዳይሸጥ መከልከል

የአህያ ቆዳ በቻይና ተፈላጊ የሆነበት ምክንያት ለባህላዊ መድሃኒት ማምረቻ ግብዓት ሆኖ ስለሚያገለግል ነው። በቢሾፍቱ ከተማ የተቋቋመው ድርጅትም የአህያ ቆዳን ለዚሁ ገበያ የማቅረብ ዓላማ እንዳለው ተገልጿል። በተመሣሣይ፣ በተለያዩ የሀገራችን አከባቢዎች የጅብ ቆዳ እና የጃርት ስጋ ለባህላዊ መድሃኒት እንደሚውሉ ይታወቃል። ስለዚህ፣ እኛ በሀገራችን የጅብ ቆዳን ለባህላዊ መድሃኒትነት እየተጠቀምን ቻይናዎች የአህያ ቆዳ ለተመሣሣይ ዓላማ እንዳያውሉ መከልከል በፍፁም አግባብ ሊሆን አይችልም።

**2 ኛ)** የበሬ ስጋን የሚበላ የአህያ ስጋን መከልከል አይችልም

ኢትዮጲያ ውስጥ የበግና የበሬ ስጋ ተወዳጅ እንደሆነ ሁሉ ቬትናም ውስጥ የአህያ ስጋ ተወዳጅ ነው። በቢሾፍቱ የተቋቋመው ድርጅትም የአህያ ስጋን ለሀገር ውስጥ ገበያ ሳይሆን ለቬትናም ገበያ የሚያቀርብ ነው። የገና እና ኢድ በዓል በመጣ ቁጥር በሬና በግ በየመንገዱና በየሰፈሩ የሚያርድ ማህብረሰብ ዘመናዊ የአህያ ቄራ በመቋቋሙ ምክንያት የሚያጣው ነገር ምንድነው? እውነት

ለመነጋገር፣ እስኪ በየከተማው ያሉ ሥጋ (ሉካንዳ) ቤቶችን ልብ ብላችሁ ተመልከቷቸው። ከምግብ ቤት ይልቅ የሰው ልጅ ጭካኔ ማሳያ እኮ ነው የሚመስሉት። የቤት እንስሳት ያለ ርህራሄ አካላቸው ተተልትሎና ተጨፍጭፎ ወደ ተሰቀለበት ሉካንዳ ቤት ሄደን ለመብላት ዘወትር የምንጎመዥ እኮ ነን። ቀን በወጣና በገባ ቁጥር የበሬ፥ በግ፥ ፍየልና የዶሮ አንገትን ያለ ርህራሄ በቢላ ስንቀነጥስ፣ ስጋቸውን ስንበላና አጥንታቸውን ስንግጥ ያልነበረ የሞራል ስብዕና ዛሬ “አህዮች በዘመናዊ ቄራ ታርደው ሥጋቸው ወደ ቬትናም ሊላክ ነው” ሲባል ከወደየት መጣ? በአጠቃላይ፣ እኛ የበሬን ስጋ እየበላን ቬትናሞች የአህያ ስጋን እንዳይበሉ መከልከል አንችልም።

**3** ኛ በአህዮቹ ላይ የመወሰን ስልጣን ያለው አርሶ አደሩ ብቻ ነው

አብዛኛው የኢትዮጲያ አርሶ አደር አንድ ውሻና አህያ ከቤቱ አይጠፋም። ምክንያቱም፣ እነዚህ ሁለት እንስሳት ከአርሶ አደሩ ኑሮና አኗኗር ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ናቸው። አርሶ አደሩ በተለይ አህያን ለገበያ የሚያቀርበው ወይ ሌላ ትርፍ አህያ ስላለው ነው አሊያም ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት ስላጋጠመው ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ በጤና እና እድሜ ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ አህዮች ሲሞቱ ጠብቆ ለጅብና ጥንብ-አንሳ ከመስጠት በስተቀር ሌላ አማራጭ የለውም። በአጠቃላይ፣ አህዮችን ከአንድ ቦታ ገዝተው ወደ ሌላ ቦታ ወስደው ከሚሸጡ ነጋዴዎች በስተቀር አርሶ አደሩ አህያን አርብቶ ለገበያ የማቅረብ ልምድ የለውም። ይህ “አህያ ሰባ ምን ሊረባ” ከሚለው የሞራል እሳቤ በተጨማሪ የእንስሳቱ የውልደት መጠን በጣም ውስን በመሆኑ ለእርባታ ምቹ አይደሉም። ነገር ግን፣ የአህያ ስጋና ቆዳ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በቢሾፍቱ ከተማ መቋቋሙ አርሶ አደሩ አህያውን በተሻለ ዋጋ እንዲሸጥ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል። በጤና እና እድሜ ምክንያት አገልግሎት መስጠት የማይችሉ አህዮችን ተንከባክቦ ለገበያ የማቅረብ እንዲችል እድል ይፈጠርለታል። በዚህም ለጅብና ለጥንብ-አንሳ ይተወው ከነበረው የአህያ ሥጋና ቆዳ ተጨማሪ ገቢ ያገኛል። በዚህ መልኩ አርሶ አደሩ አህያውን ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል። በተቃራኒው፣ ይህ ተግባር “ከእምነቴና ሃይማኖቴ ጋር አብሮ አይሄድም። ስለዚህ አህዮቹን ለድርጅቱ አልሸጥም” ካለም መብቱ ነው። በአህዮቹ ላይ የመወሰን ስልጣንና መብት ያለው አርሶ አደሩ እንጂ የተወሰኑ የከተማ አፈ-ጮሌዎችና የሃይማኖት ሰባኪዎች አይደሉም።

በአጠቃላይ፣ የእኛ ባልሆነ ንብረት ላይ የማዘዝ ስልጣንና መብት የለንም። ስለዚህ፣ አህዮቹን ለቄራ የመሸጥና ያለመሸጥ ውሳኔን ለአርሶ አደሩ መተው አለብን። ከዚህ በተጨማሪ፣ እኛ የጅብ ቆዳን ለባህላዊ መድሃኒት እንደምንጠቀመው ሁሉ ቻይናዎችም የአህያ ቆዳን መጠቀም ይችላሉ። በተመሣሣይ፣ እኛ የበሬ ስጋ እየበላን ቬትናሞች የአህያ ስጋን እንዳይበሉ መከልከል ደግሞ ተገቢ አይደለም።

ምንጭ: https://ethiothinkthank.com